# የአንድነት መርህ ይከበር ከሚሉ አባላት የተሰጠ መግለጫ

የአንድነት መርህ ይከበር የምንል አባላት የፓርቲያችን ፕሮግራምና ደንብ ተከብሮ ፓርቲው ለተነሳለት የኢትዮጵያን ህዝብ የስልጣን ምንጭ የማድረግ ዓላማ እንዲቆም የማድረግ ትግል ከጀመርን ወራትን አስቆጥረናል፡፡ በሀሳብ የተለዩ አባላትን የማስወገድና የማጥፋት ልክፍት የተጠናወተው የአንድነት ሥራ አስፈፃሚ ቡድን ግን ለውይይት በሩን በመዝጋት ህገወጥ ውሳኔዎችን እያሳለፈ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በሦስት ወቅታዊ የፓርቲያችን ጉዳዮች ላይ መግለጫ ለመስጠት ተገደናል፡፡

1. <u>አንድነት በህግ አግባብ "መድረክን" አልተቀላቀለም፡፡</u>

የአንድነት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፓርቲውን የመድረክ መጠቀሚያ ለማድረግ ከተቻለም የፓርቲውን ህልውና ከነጭራሹ ለማጥፋት የፓርቲውን መርህና ደንቦች እንዲሁም የሀገሪቱን ሕግ በተለይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000ን በማንአለብኝነት እየጣሰ ነው፡፡ ሰኔ 27 ቀን 2001ዓ.ም. "የመድረክን መለስተኛ ፕሮግራም" እና ነሐሴ 30 ቀን 2001ዓ.ም. "የመድረክን መተዳደሪያ ደንብ" ሲያጸድቅ፣ በመጨረሻም መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም. "ከመድረክ ጋር ተቀላቅሎ" አዲስ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲያቋቁምና ይህንኑም ለህዝብ በይፋ ሲያሳውቅ በተጨባጭ ለአንድነት ኘሮግራምና ድርጅታዊ ህልውና መክሰም የተስማማ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

የአንድነት ፓርቲን ዋነኛ የፖለቲካ አስተሳሰብና መርህ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻል ወይም የመለወጥ ሥልጣን የጠቅላላ ጉባዔው ብቻ ነው፡፡ የስራ አስፈፃሚውም ሆነ የብ/ም/ቤቱ "በአብላጫ ድምፅ" የመለወጥ ስልጣን የላቸውም፡፡ አንድነት የቅንጅት ፕሮግራም፣ ተስፋና መንፈስ ወራሽ እንደመሆኑ መጠንና የቅንጅትም መንፈስና ተስፋ "መሰልና አቻ" ባልሆነና ለዚህም የሚመጥን ፕሮግራምና አመራር በሌለው የፖለቲካ ቡድን በቀላሉ ሊወሰድ አይችልም፡፡ በጎሳ ፖለቲካ ቅንብርና ዕይታ የተገነባ የፖለቲካ ቡድን የቅንጅትን መንፈስና ተስፋ መተግበር እንደማይቻለው ለኛ በጣም ግልጽ ነው፡፡ "መድረክም" የመጀመሪያ የፖለቲካ ጥረቱ፣ አውቆም ሆነ ባለማወቅ፣ የአንድነት ፓርቲ መዳከም ወይም ከናካቴው መፈራረስ ከሆነ፣ ታሪኩ ሳይጸነስ የጨነገፈ ንቅናቄ ትረካ ነው፡፡

የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም "የመድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ" ነው በተባለ መግላጫ ላይ "አንድነት የመድረክን መርሆዎችና መመዘኛዎች ስለሚያሟላ መድረክን ተቀላቅሏል" የሚለው ዜና ስህተት ከመሆኑም በላይ አንድነት የመድረክን መርህ በማሟላት አባል ለመሆን ደጅ የሚጠናበት ምንም ምክንያት የለውም፡፡ ከዚሁ የ"መድረክ" መግለጫ በኋላም የአንድነት የሥራ አስፈጻሚ "መድረክን ተቀላቀልን" በማለት ለብሔራዊ ም/ቤቱ ሲያስታውቅ ሕጋዊ ዕውቅና ያለው መድረክ የሚባል የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም፡፡ እስካሁንም በህግ የታወቀ አካል አይደለም፡፡

አንድነት "መድረክን" ተቀላቅሏል በሚል እሳቤ መድረክ የወጠናቸውና እስካሁንም የፈጸማቸው ተግባራት በህግና በአንድነት አባላት ተቀባይነት የላቸውም፡፡ የአንድነት ብሔራዊ ም/ቤት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሰጠው መመሪያ ከመድረክ ጋር ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት አጥንተው አማራጭ የግንኙነት መንገዶች ለም/ቤቱ እንዲያቀርቡ ነው፡፡ ም/ቤቱም በሚቀርቡ አማራጭ ሃሳቦች ላይ መክሮ የሚስማማበትን አማራጭ ለማጽደቅ ሲሆን ይህም አማራጭ በተግባር ላይ የሚውለው ም/ቤቱ ለአንድነት ጠቅላላ ጉባዔ ካስታወቀ በኋላ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አንድነት እስከዛሬ ድረስ ከማንም የፖለቲካ ሐይል ጋር አልተቀላቀለም፤ ለሚዲያ ፍጆታና ህዝብን ለማደናገር የተለፈፈውም የአንድነትን መርህ በመጣስ የሚከሰሱት አመራሮች ጉዳይ ከመሆን አያልፍም፡፡

2. <u>በህገ ወጥ መንገድ የተጠራ ጠቅላላ ጉባኤ በፓርቲያችን ህልውና ላይ ውሳኔ ማሳለፍ አይቻልም፡፡</u>

በፓርቲያችን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10.2.4 «በማናቸውም ፓርቲውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ የመስጠት» ሥልጣን የተሰጠው የፓርቲው የመጨረሻው የሥልጣን አካል ጠቅላላ ጉባዔ በአሁኑ ወቅት

የመጠራቱ አስፈላጊነት አያጠያይቅም። ሊቀመንበራችን ወ/ት ብርቱከን ሚደቅሳ በእስር ቤት አንድ ዓመት ስታስቆጠር ፓርቲው ይህ ነው ተብሎ ሊነገር የሚችል እንቅስቃሴ ያላደረገ መሆኑና የአንድነትን ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የሚያረጋግጡ መሰረታዊ ዓላማዎቹ ተሸርሽረው ወደ ጎሳ ፓርቲነት እንዲያሽቆለቁል የተደረገ መሆኑ ለጉባኤው መጠራት በቂ ምክንያቶች ናቸው። በተጨማሪም የፓርቲ ደንብ አይገዛንም ተብሎ የፖለቲከ ውሳኔ በስፋት ተግባራዊ መሆኑ፣ የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የሚያዛቸው መመሪያዎች እንዳይወጡ ተደርጎ የጥቂት አምባገነኖች የበላይነት የሰፈነበት ህገ ወጥ አሰራር መንገሱ፣ ለአንድ አመት ያህል ሥራ አስፈጻሚው ሪፖርት ባለማቅረቡ የፓርቲው የገንዘብ አጠቃቀም በግልጽ የማይታወቅ መሆኑ፣ የ2002 ዓ.ም ምርጫ የተቃረበ መሆኑና ም/ል ሊቀመንበርና የውጪ ጉዳይ ኃላፊውን ጨምሮ በርከታ የሥራ አስፈጻሚና የብ/ም/ቤት አባላት ከፓርቲው የለቀቁ መሆኑ የጠቅላላ ጉባዔውን መጠራት ወሳኝና ወቅታዊ ያደርገዋል።

መተዳደሪያ ደንባችን በአንቀጽ 11.5 "የጠቅላላ ጉባዔውን ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል የጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴን ያቋቁማል፣ በአንቀጽ 27.1 ደግሞ «ብሔራዊ ምክር ቤቱ በሚወስነው ጊዜና ቦታ ይከሄዳል» በማለት የጠቅለላላ ጉባዔ ጥሪን ሥልጣን የሰጠው ለብሄራዊ ምክር ቤቱ ነው። ነገር ግን ይህ የብሄራዊ ምክር ቤቱ ሥልጣን ተጥሶ የጠቅላላ ጉባዔው ተሳታፊዎች ብዛትና ማንነት እንዲሁም ጊዜና ቦታው የተወሰነውና ጥሪው የተካሄደው በህግ ጥሰት በሚከሰሰው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው። ይህም ጉባዔው የአንድነትን ህልውና ለመታደግና አንድነት ያጋጠሙትን ችግሮች ለማስወገድ ሳይሆን ለህገ ወጥ ተግባራት ህጋዊ ሽፋን ለማላበስ የተጠራ ጉባዔ ያደርገዋል።

ጉባዔውን ያለ ሥልጣኑ የጠራው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ «የጠቅላላ ጉባዔው አባላት የሥራ ዘመን ሶስት አመት ይሆናል» የሚለውን የመተዳደሪያ ደንቡን አንቀጽ 10.1.8 ወደ ጎን በማለት መጠራት የሚገባቸውን የጠቅላላ ጉባዔው አባላትን ሳይጠራ በተቃራኒው የሚፈልገውን ውሳኔ ሊያሳልፉለት የሚችሉ የጉባዔ አባል ያልሆኑ ሰዎችን ጠርቷል። በአባልነት የማይታወቁ ሰዎችን በአመራርነት ለማስመረጥ በዕጩነት አዘጋጅቷል። አመራሩን በስልጣን ብልግናና በህገ ወጥነት የሚከሱት የብሄራዊ ምክር ቤት፣ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም የሥራ አስፈጻሚውን ህገ ወጥነት የተገነዘቡ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ተሳታፊ እንዳይሆኑ ተደርጓል።

በጠቅላላ ጉባዔው ለመሳተፍ ህጋዊ መብት ያለን አባላት በጉባዔው ተገኝተን የፓርቲያችንን ህልውና ለመታደግ በእለቱ ለሚገኙት የጠቅላላ ጉባዔ አባላት ያለውን ተጨባጭ እውነት የማስረዳት ኃላፊነት አለብን። ይህን ለማድረግ የስራ አስፋጻሚው ፈቃደኝነት አያስፈልገንም። ተሳታፊው የሁለት ወገን መረጃ እንዲኖረው የማድረግ ኃላፊነታችንን ለመወጣት ስንገኝ አለመግባባት ቢፈጠር ኃላፊነቱ የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ እየጣሰ በፖለቲከ ውሳኔ መንዝዝ የመረጠው ወገን መሆኑን እየገለፅን ይህ እንዳይፈጠር የአንድነት ጠቅላላ ጉባዔ፡ የብሄራዊ ምክር ቤት እና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት አስቸኳይ መፍትሄ እንዲፈልጉ ከወዲሁ አጥብቀን እንጠይቃለን። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በተድበሰበሰ ጉባዔ የፓርቲያችንን ህልውና ለማክተም የተጀመረው ጥረት ከቀጠለ የጉባዔው ውሳኔ ምንም ይሁን ምን ተቀባይነት አይኖረውም።

### 3. <u>የአንድነት ፕሮግራምና ደንብ አይሸራረፍም፣ የአንድነት መርህ ይከበር የሚሉ አባላት ቁጥር ከመቶ በላይ ሆኗል።</u>

በአንድነት ፓርቲ ውስጥ በስራ አስፈፃሚውና መርህ ይከበር በሚሉ 22 አባላት መካከል የተፈጠረውን የሃሳብ ልዩነት በሰለጠነ መንገድ በውይይት ብቻ ይፈታ የሚለውን የአብዛኛውን አባላትና ደጋፊዎች ጥያቄ በተደራጀ መልኩ በማስተባበር ጥያቄውን ለሚመለከታቸው ሁለቱም ወገኖች ለማቅረብና ውይይቱ እንዲጀመር ለማድረግ ይቻል ዘንድ በፓርቲው አባላት ተደጋጋሚ ጥረት ተደርጓል። አላማውም በፓርቲው ውስጥ በሃሳብ የተለያዩ ወገኖችን ወደ ውይይት በማምጣት ችግሩ እንዲፈታ ለማድረግ ሲሆን፣ ይህ ሊሳካ ባይችል ግን ያልቻልበትን ምክንያት እንዲሁም የትኛው ወገን ውይይቱ እንዳይሳካ መሰናክል እንደሆነ በማሳወቅ አባላትና ደጋፊዎች የራሳቸውን አቋም እንዲይዙ ለማስቻል ነው። ለዚሁ ተግባርም ከፍተኛ የጊዜ የገንዘብና የጉልበት መስዋዕትነት ተከፍሏል።

የፓርቲው አባላት ራሳቸውን በሽምጋይነት በማቅረብ በመጀመሪያ በቁጥር 14 አባላት ያሉት አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡ አስተባባሪ ኮሚቴው ከነሐሴ 2001 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በመጀመሪያ ዙር 141 በሁለተኛ ዙር ደግሞ 18 በድምሩ የ159 አባላት ፊርማን ለማሰባሰብ ችሏል፡፡ የተሰበሰበውን የ141 አባላት ፊርማ በአባሪነት በማያያዝ በ15 ቀን ውስጥ ውይይት እንዲጀምሩ መስከረም 9 ቀን 2002 ዓ.ም ለሁለቱንም ወገኖች በደብዳቤ ጠይቋል፡፡ ይህንኑ ሂደት ሊያጠናክር ይችላል በሚል እሳቤ የመድረክ አባል ናቸው የተባሉ ፓርቲዎችንና በውስጡ ያሉ ታዋቂ ግለሰቦችን ችግሩ በውይይት ይፈታ ዘንድ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ የሚጠይቅ  ደብዳቤ መስከረም 27 ቀን 2002 ዓ.ም በአድራሻቸው ተሰጥቷል፡፡ “ከመድረኩ አመራሮች” የተሰጠው ምላሽ ግን በመጀመሪያ ምንም እንዳልተፈጠረ ዝም ብሎ ማለፍ ሲሆን ቀጥሎም መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም. በፓርቲያችን ጽ/ቤት ያደረግነውን ሰላማዊ ተቃውሞ “ድግስ ማበላሸት” ብለው አባላትን እስከመዝለፍ ደርሰዋል፡፡ ይህን የተናገሩት የአንድነትን የህብረብሔራዊ ዓላማ ትቶ ከነሱጋር መቀላቀል እንደሰርግ ቆጥረውት ከሆነ የፓርቲ መርህ በመጣስና የአባላትን ድምፅ በማፈን የሚጓዙት ጓደኞቻቸው “ቅልቅል” ብቻ እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል፡፡

የተገለፁት ጥረቶችን አባላትና ደጋፊዎች አውቀዋቸው ጥረቶቹ ፍሬ እንዲያፈሩ የድርሻቸውን ማድረግ እንዲችሉ በማሰብ በተለያዩ የግል ጋዜጦች መግለጫዎች ተሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት በውይይት አመቻች ኮሚቴው በኩል የተደረጉ በጎ ጥረቶችን ውጤት በተመለከተ፤ በመጀመሪያ “መርህ ይከበር” ከሚሉ አባላት በኩል ለቀረበው የውይይት ጥያቄ ፈቃደኝነታቸውን ጥያቄው በደረሳቸው በሁለት ቀን ውስጥ መስከረም 11 ቀን 2002 ዓ.ም በላኩት የፅሁፍ መልስ በማናቸውም ጊዜና ቦታ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አባላት በታዛቢነት በሚገኙበት ለመወያየት ዝግጁ መሆናቸውን በመግለፅ አስታውቀዋል፡፡
ከዚህ በተቃራኒው ግን የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚ መስከረም 9 ቀን 2002 ዓ.ም በፓርቲው ም/ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው በኩል ተወያዩ የሚለውን ጥያቄ በአክብሮት ተቀብለው በቃል በአጭር ቀን መልስ እንደሚሰጡ ቃል ገብተው የነበረ ቢሆንም በተግባር ግን በኢሜልና በጋዜጦች የስም ማጥፋት ዘመቻ በመክፈት “ችግራችሁን በውይይት ፍቱ” ከሚለው ግልፅና ቀጥተኛ ጥያቄ ጋር የማይዛመድ መልስ በመስጠት እርሳቸው የሚመሩት ቡድን በፓርቲው ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ዋናው ተዋናይ እንደሆነና የአንድነት አባላት እውነቱ የት እንዳለ እንዲታወቅ አድርገዋል፡፡

በመሆኑም በውይይት አመቻች ኮሚቴውና በአባላት ድጋፍ የተደረገው ጥረት ሁሉ ለመወያየት ዝግጁ ባልሆነውና የፓርቲውን አባላት ሥም በሃሰት በመወንጀል በተጠመደው የሥራ አስፈፃሚው ቡድን ምክንያት ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ ኮሚቴውም የሽምግልናው ሂደት ያለውጤት የተጠናቀቀ መሆኑንና የኮሚቴውም ህልውና ያከተመ መሆኑን የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች እንዲያውቁት መግለጫ በማውጣት ተጠናቋል፡፡ ሂደቱ ግን የችግሩን ምንጭና አሳሳቢነት በሚገባ አሳይቶናል፡፡ ከዚህ በኋላ ፊርማ በማሰባሰብ በሽምግልናው አካል የነበሩ የአንድነት የብሄራዊ ም/ቤት፣ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን፣ እንዲሁም በዞንና በወረዳ በተለያዩ የፓርቲው የአመራር ደረጃ የሚንቀሳቀሱ አባላትን ጨምሮ በርካታ መስራች አባላት የፓርቲያችንን መርህ ለማስከበር በመወሰናችንና በአንድ ላይ ለመስራት በመስማማታችን መርህ ይከበር የምንል አባላት ቁጥር 102 ደርሷል፡፡ ወደፊትም አባላት የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ከጎናችን እንዲቆሙና የፓርቲያችንን ህልውና ተባብረን እንድናስከብር ጥሪያችንን እያስተላለፍን፣ እኛም የፓርቲያችን መርህ መከበር እስኪረጋገጥ ትግላችን ይቀጥላል፡፡

የአንድነት መርህ ይከበር ከሚሉ አባላት
ህዳር 12 ቀን 2002 ዓ.ም.